# ከወሬ ፋብሪካነት ይሰውራችሁ!

ሰላም ሰላም! እንዴት አላችሁልኝ? እንዴት ነው አገሩ? አየሩ? ልማትና ግሽበትስ? መቼም መጨመር የምትባለዋ ነገር ራሷ ‹‹ልማታዊ›› ሳትሆን አትቀርም መሰለኝ አንድም የሚቀንስ ነገር ጠፍቷል። ልማት ኑሮን ቀለል፣ ላላ፣ ዘናና አስደሳች ያደርጋል እንጂ፣ ከመቼ ጀምሮ ይሆን ውጥረት በውጥረት የሚያደርገው? የጠየቅኋችሁ ስለማላውቅ እንጂ ለሌላ አይደለም ኢደራ። ዘንድሮ እኮ አለማወቅም ራሱ ጨምሮላችኋል። እውነቴን እኮ ነው! ያው ሳያውቁ፣ ሳይመረምሩና ሳይረዱ አዋቂ መምሰል በዝቷል ማለቴ ነው። የሆነ ነገር ስታወሩ ዝም ብሎ ሲያዳምጥ የቆየ ሰው ‹‹I know›› ይላችኋል። ካወቅክ ምን አስለፈለፈኝ ብላችሁ ዝም ብትሉት ‹‹ጨዋታህን አቋረጥከውሳ›› ብሎ ለንዝንዝ ይነሳል። እሺ አሁን ይኼን ምን ትሉታላችሁ? ‹‹ዲስኩር ያሳበጠው ሁሉ ከላይ እስከታች ተሰብስቦ ነገሩን በሙሉ የልጅ ጨዋታ አድርጎት ይረፈው? መጥኔ!›› ይሉ የነበሩት ባሻዬ ሰሞኑን ድምፃቸው ጠፍቷል፡፡

በነገራችን ላይ በዚህ ቀውጢ የግሽበት ጊዜ አንድ ‹‹ቀንሼያለሁ›› የሚል ተገኝቶ የተገረምን አልጠፋንም። ብር አይደለም ሽራፊ ሳንቲም አይምርም ይሉታል የሠፈሬ ልጆች። ለእኛ ለደላሎች ትልቁ ወጪያችን የሞባይል ካርድ ነው። ‹‹ቀንሶላችኋል›› ሲባል ግን ምንም ሳይደንቀኝ ቀረ። ‹‹ታሪፍ›› ተቀነሰ ሲባል ደንገጥ ማለት ቀረ እኮ፡፡ ለምን አትሉም? ያው ከነዳጅ የተኮረጀች ‹‹ቅነሳ›› ሳትሆን አትቀርም ተብሎ እየታሰበ እኮ ነው። በአምስትና በአሥር ሳንቲም ቅናሽ ልባችንን እየሰቀለና እያወረደው ባለው የዋጋ ቅናሽ ተስፋ ቁርጥ አድርጌ ተውኩት። እውነቴን ነው እናንተም እርማችሁን እንድታወጡ በወንድምነት ልምከራችሁ። ያው ሰው ሲሞት ካልሆነ እርም ማውጣት አልተለመደም ብላችሁ መሸወድ ያለባችሁ አይመስለኝም። ቢቻል በቁማችን እየተያየን ‹‹ይብላኝልህ ይብላኝልሽ›› ብንባባል ጥሩ ነበር። አዎ መንግሥታችንንም እየታዘብነው ሳይሆን እያዘንለት ‹‹ይብላኝልህ›› ብንለው ‹‹ልማታዊ›› አዛኝነታችንን ገለጽንለት ማለት ነው። ‹‹ሃሃሃ›› እያልኩ እንዳልስቅ ውስጤ እንደማሽላ እያረረ ነው፡፡

ይገርማችኋል አንዳንዱ ከዘንድሮ ቆንጆ ቆንጆ ልጃገረዶች በርከት አድርጎ የስልክ አድራሻ የተቀበለ ይህን የቴሌኮም ታሪፍ ቅናሽ ሰምቶ አላስቆም አላስቀምጥ ብሏል የሚል ነገርም ሰማሁ። ይህ ትልቅ ትዝብት ውስጥ የሚከት መሆኑን ከባሻዬ ልጅ ጋር አንስተን ተጫዋወትን፡፡ ታሪፍ ቀነሰ ተብሎ ለሥራ ጉዳይ በአግባቡ ልንጠቀምበት የሚገባንን በፍሬ ፈርስኪ ወሬ ማባከን አያዋጣንም ጎበዝ! ዋ ምን ይታወቃል ያለ አግባብ ካርድ በማባከንና በመሰል ራስን ጎጂ የሆኑ ጉዳዮች ‹‹ኪራይ ሰብሳቢ ወይም ኢ ልማታዊ›› ተብለው ቅጽል ሊወጣላቸው ይችላል፡፡ ኧረ በቅጽል ብቻ የማይታለፉም አሉ። ልብ ያለው ልብ ይበል። የሞባይል ስልክ ጉዳይ ሲነሳ ገና አገልግሎቱ እንደተጀመረ ሰሞን አንዷ የማይከፈልበት ይመስል በወር የሚከፈልበትን ስልክ ስትቀጠቅጥ ትከርምና ቢል ሲመጣ አሥር ሺሕ ብር ክፈይ ትባለለች፡፡ ደንግጣ ‹‹ይኼ ሁሉ ሒሳብ ከየት መጣ?›› ብትል ‹‹ምናልባት ዘፍነሽበት ይሆናል›› አሏት ተብሎ ተወራ አሉ፡፡ አቤት ወሬ?

ይገርማችኋል እኔ ደላላው አንበርብር ምንተስኖት በአጉል ወሬ አላምንም፡፡ ይኼ ከላይ ነካ ነካ ያደረግኩት ለጨዋታ ያህል መሆኑን አጢኑልኝ፡፡ ይኼን አለ ተብዬ ደግሞ መቆሚያና መቀመጫ ልጣ? ሆሆ! ድሮ ሰው ፀጥታውንና ሰላሙን ያጣ የነበረው አገሩ በጠላት ስትወረርና አስመራሪው ረሃብ ከደጃፉ ከደረሰ ነበር፡፡ አሁን ግን የሰው መጥፊያው አፉ ሆኗል አሉ። በተለይ ወሬ፡፡ በእርግጥ አንዳንዶች በማስረጃ የተደገፈ ክስ የተመሠረተባቸው ናቸው ተብሏል። እነሱ ሥራቸው ስለሚመሰክር እኔን አያገባኝም። ምን ነበር እ .. . አዎ ‹‹እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል›› ተብሏል እኮ። ኧረ ምን ያልተባለ አለ? ‹‹ጉድና ጅራት ከበስተኋላ ነው›› ሲባልስ ያልሰማ አለ? አንድ ጊዜ አንዱ ተከሶ ፍርድ ቤት ቀረበ አሉ፡፡ ዳኛው ቆጣ ብለው ‹‹ጥፋተኛ ነህ አይደለህም?›› ሲሉት፣ ከሳሹን እየገላመጠ ‹‹ልጅ ከሳሽ አባት ዳኛ በሆኑበት እንዴት አላጠፋሁም እላለሁ?›› አለ አሉ፡፡ ዳኛው እየሳቁ ‹‹ተሳስተሃል እኔ አጎቱ እንጂ አባቱ አይደለሁም፡፡ ስም በማጥፋትህ ደግሞ ትቀጣለህ፤›› ብለው ከርቸሌ ላኩት ተብሎ ተወርቷል፡፡ ሰው በቃ ያለወሬ ነገር የለውም?

እናም መልካም ተብላ የተነገረች ወይም ጣል የተደረገች ጨዋታ መሰል ወሬ ስንቱን ወዳጅ፣ ዘመድ፣ ጎረቤትና የሥራ ባልደረባ አቀያየመችው መሰላችሁ? እኔማ አንዳንዴ ማንጠግቦሽ ጎድን የምትከተክትበትን ቢላዋ እንደ ጎራዴ እያወዛወዝኩ ልፎክር አስብና እተወዋለሁ፡፡ ይኼን ያየ አንዱ ይነሳና ‹‹አንበርብር ሊሸፍት ነው›› ብሎ ቢያወራስ? የእኔ ሽፍትነት ግፋ ቢል ከመርካቶ ወይ ከቄራ እንደማያልፍ እየታወቀ መዘዙ ሌላ ሊሆን ይችላል፡፡ ብቻ መጠርጠር ደግ ነው! ‹‹በለፈለፉ በአፍ ይጠፉ›› በሚሊኒየማችን በግልጽ እንደታየ ለማስታወስ መቼም እንደ ኢቲቪ ‹‹ዶክመንተሪ ፊልም›› መሥራት አይጠበቅብኝም። ይጠበቅብኛል? ኧረ በጭራሽ፡፡

መቼም ከተነሳ ላይቀር ኢቲቪ ዶክመንተሪ ፊልም መሥራት ይወዳል ብቻ ሳይሆን፣ ካልሠራ ያቃዠዋል ሲባል ሰምቼ እነግራችኋለሁ ስል ይኼው ረስቼው ነበር። የባሻዬ ልጅ፣ ‹‹ዶክመንተሪ ፊልም ኢቲቪ ጠላቶቹን ድባቅ መምቻ ጎራዴው ነው፤›› አለኝ። እኔ ግን ግራ ገብቶኝ ኢቲቪ ደግሞ የምን ጠላት አለው? መጀመርያውኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሚዲያ እንጂ የየትኛው ድርጅት የገደል ማሚቶ ሆነ? ብዬ አሰላሰልኩ። ብዙም ሳልቆይ ግን የአገራችን ‹‹ጠላቶች›› ብዛት ታወሰኝና ነገሩ ገብቶኝ ተውኩት፡፡ አዎ! ማለፍ መልካም ነው! ‹‹እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል›› ይላሉ ባሻዬ ከነገር ሲሸሹ፡፡ እኛ ግን ከነገር ሳይሆን ከአጉል ነገር ላይ ገልበጥ ብለን ብንቀየስስ? ‹‹ያልተገላበጠ ያራል›› ሲባል አልሰማችሁም? የሐበሻ ልጆች ሆናችሁ ይህን አታውቁም ማለት ንቀት ስለሆነ ይቅርታ እጠይቃችኋለሁ፡፡

እስኪ ሰሞኑን በጣም አስቀይሞኝ የነበረውን ነገርና የሆንኩትን ላጫውታችሁ። ያስቀየመኝ አንድ አስተያየት ሰጪ ነው። የሊዝ አዋጁን አስመልክቶ በአዲስ አበባ ከንቲባ ሰብሳቢነት በተደረገው ውይይት ላይ የተሳተፈ አንድ ሰው ‹‹አዋጁን ብናውቀው ይጠቅመናል! በአሁን ጊዜ ለመንግሥት የምንከፍለው ለደላላ የምንከፍለውን አያክልም፤›› ብሎ አረፈው። እኔ የፈለገውን ቢያወራ ምንም ግድ ባላለኝ፡፡ ነገር ግን ደላላ ሠርቶ እንደማይበላ ሁሉ እንደዚህ ስንባል በእጅጉ አንገፍግፎኝ ራሴን ጠላሁት። ምን ዋጋ አለው ብላችሁ ነው? ወኔና ብርታት ዋጋውን አንረውት ኖሮ ራስን መጥላትም ተወዶ አርፎታል፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ‹‹ፀረ ደላላ›› የወሬ ቱማታ ከሰማሁ በኋላ ምርር ብሎኝ ባሻዬ ዘንድ ሄድኩ። ነገሬን ሲረዱ፣ ‹‹ቱ ቱ! የሰይጣን ጆሮ አይስማው እቴ! ምነው አንበርብር ምነው? ሰው በስንቱ ተስፋ ቆርጦ ይችላል?›› እያሉ አበርትተውኝና መክረውኝ ተመለስኩ፡፡ ግን ሰው በስንቱ ተስፋ ቆርጦ ይችለዋል? እስኪ አስቡት! መተሳሰብና መተዛዘን በጠፋበት ዘመን ይሉኝታ ቢስነት ሲጨመርበት ተስፋ አያስቆርጥም? ራስ ወዳድነት ተንሰራፍቶ ሙስና ጣርያ በነካበት በዚህ ዘመን ተፈላላጊዎችን አገናኝቶ ንግድን ‹‹ማሳለጥ›› በወሬኞች ሲወገዝ ምን ይባላል?

ስለ ተስፋ መቁረጥ ሳወራ የልዕለ ኃያሏ አሜሪካ አለቃ ባራክ ኦባማ ትዝ አሉኝ፡፡ ‹‹አይ ዘንድሮ እንጃ! ሰውዬው ተስፋ ቁርጥ ያደረጉ ይመስላል፤›› ብሎ ያጫወተኝ የሰሞኑን የአሜሪካን የምርጫ ቅስቀሳ መቃረብ በተመለከተ ቴሌቪዥን ላይ አፍጥጦ የሚውለው የባሻዬ ልጅ ነው። ‹‹ምስኪን

ኦባማ ለውጥ ለውጥ ብለው ፎክረው አንድ ያያንላቸው ነገር ቢኖር ጥቁር ፀጉራቸው ወደ ነጭ መቀየሩን ነው፤ እንደጉድ ሸበቱ፤›› ብሎ ሲያስቀኝ ሰነበተ። ‹‹ያን ያህል ምንም አልሠሩም ብሎ ማለት የለየለት ጥላቻ ነውና እንዲህ የሚባሉ ሰው አይደሉም፤›› ብዬ ግን ሞገትኩት። እውቴን አይደለም? የሚያጠፋ እኮ የሚሠራ ሰው ነው እናንተዬ! በእርግጥ ጥፋት ይኖራል። ነገር ግን ስለተሠራውና ስለተጠበቁ ቃሎች ያው ሰው መመስገን ይገባዋል ባይ ነኝ። እንዲህ ስል የሰሙኝ የሠፈር ሰዎች ‹‹አንበርብር የዓመቱ ልማታዊ አመስጋኝ ተብሎ መሸለም ይፈልጋል፤›› ብለው እንዳሙኝ ሰማሁ። ‹‹ይብላኝ ለወሬኛ አፉን ለማይበላው፤ ለወሬ የለውም ፍሬ፤›› ብዬ መልዕክት ላኩባቸው። ምድረ ሐሜተኛ ልክ ልኩ ካልተነገረው እኮ አገሪቱ የወሬ ፋብሪካ መሆኗ ነው፡፡

‹‹አይ አንበርብር ኦባማ ሰሞኑን ያሉትን አልሰማህም ማለት ነው? ካሁን በኋላ የዓለም ልዕለ ኃያልነታችንን የምናረጋግጠው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተራቀቀ ጦር ኃይል ሲኖረን ነው አሉ። እኔ በበኩሌ ከእሳቸው ይኼን አልጠብቅም ነበር፤›› አለኝ። ‹‹ምን ያድርጉ? እነኢራን ልባቸው አብጦ አስደነገጧቸው። ይህች ባቄላ ካደረች እያሉ ብቅ ላለው ሁሉ መሸበር ለጤናቸውም ደግ አይደለም። በሌላ በኩል ሥልጣን ላይ ለመቆየት ምንም ማስተማመኛ የላቸውም። ወንበር የማይጣፍጠው ማን አለ ብለህ ነው? የትም ሂድ የት ሥልጣን ለማንም የዛፍ ላይ እንቅልፍ እየሆነ ነው፤›› አልኩት፡፡ የባሻዬ ልጅ በማብራሪያዬ ተገርሞ ሲያየኝ ቆየና ‹‹ከአህያ ጋር የዋለች ጊደር . . . ›› ብሎ ሳይጨርስ በሳቅ ወደቅን። ግን እውነቴን ነበር የተናገርኩት። አይደለም እንዴ? ሁሌ መባከን እኮ ነው፡፡ እኛ አገር አማን ብለን ወጥተን ስንገባ እነሱ በበረገጉ ቁጥር እንተረማመስ እንዴ? ከዛፍ ላይ እንቅልፍ ያላቃቸው! በርግገው ከማስበርገግ ይገላግላቸው እንጂ ሌላ ምን ይባላል? ምንም!

እንዲያው ቸር ወሬ ያሰማን ነው የሚባለው መቼም:: የሰው ልጅ ምን ቢማር ምን ቢመራመር ሰላምን ማስፈን አልቻልበት ብሎ ጦር ሲያንጋጋ ማየቱን ለምድነው ምንም የማይመስለን? ሠለጠኑ የሚባሉ አገሮች ጡንቻቸውን እየወጣጠሩ የእኔ ይበልጥ ያንተ ያንስ ሲባባሉ ማየት በጣም ያሳፍራል። ‹‹ያው መሆን አይቀር›› አለ ያገሬ ሰው። ግን ዋናው ቁምነገር እኛ ምን እንማራለን የሚለው ነው። አፍሪካውያን ስንባል በቁማችን የሞትን፣ ዓይናችንን ቢጠነቁሉን የማይሞቀንና የማይበርደን አድርገው ሲያስቡን፣ መልሰው እኛን በሚያሙበት ነገር እነሱም ራሳቸው ሲተራመሱ ማየት ወይ ጊዜ ያስብላል። ታዳያ ብልጥ መሆን ያለብን አይመስላችሁም? የዲሞክራሲ፣ የኢንዱስትሪ፣ የማዳበሪያ፣ ወዘተ ተሞክሮአቸውን ብቻ ከምናጠና ይኼ የጉልበት አስተሳሰብና እኔ እበልጥ ጥላቻ አዘል ሸኩቻ እንዴት ገጽታ አበላሽ እንደሆኑ ብንማርባቸው ደግ አይመስላችሁም? ዝንት ዓለማችንን ምሳሌ ሲያስነግሩብን ኖረን ማለፍ ያለብን አይመስለኝም። ለዚህ መድኃኒቱ ከወሬ ቀነስ፣ ከሥራው ጠበቅ ማለት አለብን፡፡ ዲሞክራሲ በሌለበት ባዶ ቱሪናፋ፣ መልካም አስተዳደር በሌለበት የውሸት ቱልቱላ፣ የሚበላ በሌለበት የጥጋብ ፕሮፓጋንዳ፣ እኩልነት ባልሰፈነበት የሐሰት ሐተታ፣ መብት በማይከበርበት የማይመስል ወሬ የትም አያደርስም፡፡ ከወሬ ፋብሪካነት ይሰውራችሁ፡፡ ራዕይ ያለው ሕዝብ አይጠፋምና በርቱ ተበራቱ። መልካም ሰንበት!